የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

ለኢትዮጵያ አንድነትና ዴሞክራሲ

**ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር (ኢሕአግ)**
**አለም አቀፍ ኮሚቴ፤**
**<u>የተሰጠ መግለጫ</u> ኦገስት 30 ቀን 2007**

## <u>መግቢያ፤</u>

የኢሕአግ አለም አቀፍ የውጭ ኮሚቴ ትግሉን በተደራጀ መልኩ በይፋ ከጀመረበት ከሜይ 2006 ጀምሮ ባደረገው እንቅስቀሴ፣ በአጠቃላይ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከወያኔ መራሹ ውድመት ለማዳን፤ ኢሕአግ እና ሌሎች ለተመሳሳይ አላማ የተደራጁ ሃይሎች የሚገኙበትን ሁኔታ፣ የጎረቤት አገሮችን አሻጥርና ትርምስ፣ የአርበኛውን ገድልና ትግሉ እንዳይጠናከር ተብትቦ የያዘውን ችግር በአሉባልታ ሳይሆን እራሳችን በመሳተፍ በቅርበት ለማየት ችለናል።

የዚህ መግለጫ ዋና ዓላማ ቀደም ሲል ለሕዝብ ይፋ ባደረግነው መሰረት በኢሕአግ አመራር፣ አደረጃጀትና ድርጅታዊ ነፃነት ዙሪያ የተመለከትናቸውን ችግሮች በማጥናት የመፍትሄ ሃሳብ የሚያቀርብ «የችግሮች ጥናትና መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ» ተቋቁሞ ያቀረበውን ሰነድ መሰረት በማድረግ ከዚህ ጥናት መጠናቀቅ በኋላ ተግባራዊ የሆኑትንና መፍትሄ ያልተገኘላቸውን ችግሮች፣ በገባነው ቃል መሰረት ለሕዝብ ለመግለጽና የኢሕአግን እጣ ፋንታና ቀጣዩን የትግል አቅጣጫ ለደጋፊዎቻችንና ለሕዝባችን ለማሳወቅ ነው። ጹሁፉ በአጭሩ የተዘጋጀና አጣዳፊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ብቻ ሲሆን፤ ዝርዝር ጉዳዮችን በሚመለከት «ኢሕአግ ከየት ወዴት» በሚል እርስ ጥናታዊ ጹሁፍ እዬተዘጋጀ ስለሆነ የተሟላ መረጃዉ ወደፊት ይቀርባል።

ለግንዛቤ ይረደ ዘንድ መግለጫው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

ክፍል 1 - የግንባሩን ችግሮች ለማስወገድና ትግሉን ለማጠናከር በአለምአቀፍ የውጭ ኮሚቴው የተደረጉ ጥረቶችና የተመዘገቡ ውጤቶች፣

ክፍል 2 - በተለያዩ ምክንያቶች ሊወገዱ ያልቻሉ ወሳኝ የግንባሩ ችግሮች፣

ክፍል 3 - የዓለምአቀፍ ኮሚቴው ውሳኔዎችና ቀጣዩ «አገርን የማዳን» የትግል አቅጣጫ፤

## ክፍል 1፤

### የግንባሩን ችግሮች ለማስወገድና ትግሉን ለማጠናከር በአለምአቀፍ የውጭ ኮሚቴው የተደረጉ ጥረቶችና የተመዘገቡ ውጤቶች፣

### 1.1 የግንባሩን ዋና ዋና ችግሮች ለይቶ በማጥናት ችግሩ የሚወገድበትን የመፍትሄ ሀሳቦች አቀርበናል::

የአለምአቀፍ ኮሚቴው በተደራጀ መልኩ ትግሉን ለማገዝ መንቀሳቀስ በጀመረ በጥቂት ወራቶች ውስጥ፤ ኢሕአግ በአንድ በኩል መሪና የሠራዊት ዋና አዛዥ የተባለው መስከረም አታላይ፤ በውጭ አገር ስደተኛ ከምፕ ውስጥ ለሁለት አመት ከትግሉ እርቆ መቆየቱ ብቻ ሳይሆን፤ የግንባሩ አመራር ሳያውቅ በምስጢር የፖለቲክ ጥገኝነት በአውሮፓ መጠየቁና እመራዋለሁ ወደሚለው አርበኛ ለመመለስ ፍቃደኝነት ባለማሳዬቱ፤ በሌላ በኩል በግንባሩ ዋና ጽ/ቤት አካባቢ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ነው የተባለዉ ሙሴ ተገኝ፤ ለአርበኛው የተላከለትን የእርዳታ ገንዘብ አለማድረሱና ግንባሩን በረቀቀ ዘዴ በመከፋፈል እያዳከመው መሆኑን በመገንዘባችን፤ የግንባሩ ድርጅታዊ ነፃነትና፤ በአርበኛው የሰብአዊ መብቶችም በኩል ምሁራንና ጠንካራ የኢትየጵያዊነት ስሜት ያላቸው እየተመረጡ እንደሚታሰሩ አደጋ ላይ እንደሚወድቁ በመገንዘባችን፤ «የችግሮች ጥናትና መፍትሄ አፈላላጊ» ኮሚቴ በማቋቋም ዝርዝር ጥናት ከእነ መፍትሄ ሃሳቦች ከስምንት ወራት በፊት አቅርበናል::

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጭብጦች በከፊል ለሕዝብ ይፋ ማድረጋችን የማታወስ ሲኖን፣ አሁንም በድረ-ገፃችን ( www.eppf.info) ላይ ይገኛል:: የዚህን ጥናት ውጤት ተግባራዊ ማድረግ የመቻሉና ያለመቻሉ ጉዳይ የግንባሩን ሕልውና የሚወስን መሆኑን በገለጽነው መሰረት፤ ለተግባራዊነቱ ከስምንት ወራት በላይ በጽናትና በትግስት ስንታገል ቆይተን፣ አሁንም ካለንበት አቋም ላይ ደርሰናል::

### 1.2 በጥናቱ ከቀረቡት ዋና ዋና ችግሮች መከከል፤ አለምቀፍ ኮሚቴውና በየቻፕተሩ የተደራጁ አባሎችና ደጋፊዎቻችን ባደረጉት ያላሰለሰ ትግል የሚከተሉት ተግባራዊ እንዲሆኑ አስችሎናል::

#### 1.2.1 የመስከረም አታላይ ክህደት፤ ቅጥፈትና ትግሉን የመግደል እቅድ መጋለጥ፣

መስከረም አታላይ ግንባሩን ሆን ብለዉ ለማዳከምና ለመግደል ታጥቀው ከተነሱት የውጭና የውስጥ ሃይሎች ጋር በማሴር፤ ኢሕአግ አሁን ለሚገኝበት ውድቀትና ቀውስ አስፈጻሚና ፈጻሚ በመሆን ብቻ ሳይወሰን፤ እራሱን በአውሮፓ ስደተኛ ከምፕ ውስጥ ደብቆ ለሁለት ዓመታት ከአርበኛው ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ሳይኖረው፤ እራሱን አዋጊ፣ አድራጊና ፈጣሪ አድረጎ በማቅረብ፤ እውነት መስሏቸው ትግሉን ሊረዱ የተዘጋጁ ኢትዮጵያዉያንን ቅስም የሰበረ፣ ትግል ገዳይና ጥቅም ፈላጊ ግለሰብ ነው:: ይሁን እንጂ ለእውነተኛና ቆራጥ የኮሚቴያችን አባሎች ምስጋና ይግባቸውና ይህ ቅጥፈትና ትግልን የመግደል ሴራ በፍጥነት ተጋለጦ በተደረገው ግፊትና ትግል የግንባሩ አመራር ሳይቀር መስከረም አታላይ ከሃላፊነቱ መወገዱን በይፋ መግለጫ አውጥቶበታል:: መስከረም አታላይና አጃቢዎቹ ትላንትና እኛን ከኤርትራ ጋር ሊያጣሉ ታጥቀው የተነሱ አክራሪዎች ብለው እንዳልከሰሱን ሁሉ ዛሬ ደግሞ ከተባረሩ በኋላ መልካቸውን ቀይረው ከትብበር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ (ኤ ኤፍ ዲ) ወጥተናል፤ በኤርትራ በኩል ትግል አይቻልም፤ እያሉ ዋና ጽ/ቤታቸውን በጀርመን ስደተኛ ከምፕ አድርገው በትግል ስም መቀለድ ቀጥለዋል::

ይህ የማፈንገጥ ሙከራ ከአልተገታና የከፍተኛ ታጋዬችን ስም መጉዳት ከልቆመ የሚጋለጡበት በቂ ማስረጃ ስለአለን ለሕዝብ ለማቅረብ እንገደዳለን::

**1.2.2** <u>ከውጭ ሀይሎች ጋር ለብዙ ዓመታት ተጣብቀው ኢሕአግን ለውድቀት የዳረጉት ሌሎች አባሎች እንዲጋለጡና ከግንባሩ እንዲለቁ አድርገናል</u>።

በታጋይነት ስም ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር፤ ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት፤ ከአንድ ፓል ቶክ መድረክ ወደ ሌላ ፓል ቶክ መድረክ፤ እየተገለባበጡ በፈጠራ የአሉባልታ ወሬ የታጋዬችን ስም ሲያጠፉ፤ የቻሉትን ስያስባርሩ፤ ሲያሳስሩና ሲከፋፍሉ፤ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ ትግሉን የማዳከም፤ ታጋዮችን ግራ የማጋባት ሴራ ሲጠነስሱ የነበሩትን የኮሚቴ አባላት፤ ከኮሚቴያችንና ከግንባሩ እንዲለቁ ለማድረግ ተችሏል። አንዳንዶቹ እንደገና ተገለባብጠው ሌላ ሴራ ከመጎንጎን እንደማይቆጠቡ ብናውቅም ርቃናቸውን በመቅረታቸው ያሉትን ቢሉ በማንኛውም ሕዝባዊ መድረክ ተሰሚነት እንደማይኖራቸው እርግጠኞች ነን።

**1.2.3** <u>የአርበኛ ድምጽ ራዲዮ ሥርጭት በሥራ ላይ ውሏል</u>።

ይህ በ 15260 ኪሎ ኅረዝ 19 ሜትር ባንድ አጭር ሞገድ ዘወትር ሐሙስ ከምሽቱ አንድ እስከ ሁለት ሰዓት ወደ ኢትዮጵያና የአከባቢዉ አገሮች በቀጥታ የሚተላለፈው ስርጭት ሕዝቡን ለትግል ለማነሳሳት ከሚሰጠው ጥቅም በተጨማሪ፤ ኢሕአግን ከተበተበው ውስብስብ ችግር ለመውጣት የተነደፉ መፍትሄ ሀሳቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ድርሻ እንዲኖረው በሚገባ ታቅዶ የተጀመረ ፕሮግራም ነው። እንደታሰበውም ግንኙነታቸውን ከእኛ ጋር ለወራት አቋርጠው ያደፈጡት የኢሕአግ አመራሮች ለተከፈተው ራድዮ እውቅና በመስጠትና በጥናታችን የቀረቡትን የመፍትሄ ሀሳቦች ተቀብለው ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ መቀራረብና የውይይትና ድርድር መድረክ በር ከፍቶ ነበር። የራዲዮ ስርጭቱ አሁን ለደረስንበት ወሳኝ የትግል ደረጃ በሚመጥን መልኩ በስፋትና በጥራት እንዲቀጥል ዝግጅት እየተደረገ ነው።

**1.2.4** <u>አስተማማኝ ድረ-ገጽ (www.eppf.info) በሥራ ላይ ውሏል፤</u>

ይህ ድረ-ገጽ ለሁለገብ ትግሉ ጠቀሜታ ያላቸውን መረጃዎች ለሕዝብ በፍጥነትና በጥራት ለማሰራጨትና፤ የወያኔን ግፍና በደል በማጋለጥ ላይ ያተኮረ ሆኖ የተደራጀ ነው። ከተሞክሮ እንዳየነው የድረገጽና ሌሎች ሚዲያዎች ያለምንም ተጽእኖ እዉነተኛ መረጃ ማስተላለፍ በሚችሉበት ሀኔታ መደራጀታቸው ለትግሉ ወሳኝ ስለሆነ በተጠናከረ መንገድ ይቀጥላል።

**1.2.5** <u>የትግሉን አድማስ ለማስፋትና ለማቀናበር ተስፋ የሚሰጡ ተግባሮች ተከናውነዋል</u>።

በተመሳሳይ ትግል ላይ ከተሰማሩ የተለያዩ ወገኖች ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ ትግሉን ለማቀናጀትና ውጤታማ እንቅስቃሴ ለማድረግ አስተማማኝ የሆነ መሰረት ተጥሏል። ዝርዝር ሁኔታውን በዚህ ጹሁፍ ማቅረቡ ትግሉ ላለበት ደረጃ ስለማይጠቅም፤ በአጭር ግዜ ውስጥ የሚታይና የሚዳሰስ ዉጤት እንደሚታይ ተስፋ እናደርጋለን።

**1.2.6** <u>የዓለምአቀፍ ኮሚቴውና የድጋፍ ቻፕተሮችን በጥራትና በረጂም ጊዜ የዓላማ ግብና ጽናት ላይ በተመሰረተ መልኩ ለማደራጀት መሰረት ተጥሏል</u>።

በቀረበው የጥናት ሰነድ ላይ ያቀረብናቸው ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ ሆኑም አልሆኑ ወደ ትግሉ ስንገባ የተነሳንበት ዓላማ ማለትም «ኢትዮጵያንና ኢትየጵያዊነትን» የማዳን ታላቅ ብሄራዊ ዓላማ ግቤ ላይ አስከምንደርስ ድረስ፤ ለጥፋትና ለውድመት የታጠቀና የተደራጀን ሃይል፤ ማሸነፍ የሚቻለዉ ይበልጥ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ ሀይል ብቻ ነውና ለጠንከራ ሕዝባዊ አደረጃጃት መነሻ የሚሆኑ የቻፕተሮች ማቋቋሚያ ሕገ-ደንብና የአለምአቀፍ ኮሚቲው ጊዜያዊ መተዳደሪያ ደንብ ጸድቆ በሥራ ላይ ውሏል። ትግሉን ሕዝባዊ ለማድረግ የተጀመረው አደረጃጀትም በስፋት ይቀጥላል።

## <u>ክፍል 2፤</u>

### በተለያዩ ምክንያቶች ሊወገዱ ያልቻሉ ወሳኝ የግንባሩ ችግሮች፣

የዓለምአቀፍ የውጭ ኮሚቴው ለይቶ ያቀረባቸው ኢሕአግን ተብትበው የያዙት ችግሮች እንዲወገዱና የኢትዮጵያ ሕዝብ በተስፋ የሚጠብቀውን «አገርንና ሕዝብን» ከጥፋት የማዳን ተልእኮ በብቃት እንዲወጣ ለማድረግ ባለፉት ስምንት ወራት በተደረገው ትግል ከላይ በክፍል 1 የተዘረዘሩትን ውጤቶች ያስገኘ ቢሆንም፤ ግንባሩ የወደፊት እጣ ፋንታውን ከሚወስኑት አብይት ችግሮች ግን ገና አልተላቀቀም። የእኛ እንቅስቃሴ በተቻለ መጠን ጠላትን በማያስደስትና፤ የወገንን ተስፋ በማያጨለም፣ በእስር ላይ የሚገኑ አርበኞችን አደጋ ላይ በማይጥል መንገድ እያጠናን፣ ግፊቱንና ትግሉን በመቀጠል ጎን ለጎን ሌሎች አማረጮችም ተጠንተውና ተገምግመው ትግሉ ሳይኮላሽ የሚቀጥልበትን መንገድ በማመቻቸት ላይ በማተኮራችን ደጋፊዎቻችን በጠበቁትም ሆነ የራሳችን ህሊና በፈቀደው ፍጥነት የኢሕአግን እጣ ፋንታ በይፋ ለማቅረብ ያለመቻላችንን እየገለጽን፣ እንቅስቃሴያችንን ስትከታተሉ የቆያችሁ ወገኖች ምክንያቱን እደምትረዱልን አንጠራጠርም። በአሁኑ ወቅት ማስተካከል ያልቻለውንና ምንም ያህል ትግል ብናደርግ መለወጥ ያልቻላቸውን ችግሮች በሚገባ ለይተን በማወቃችንና፤የታሰሩት አረበኞችም ሁኔታ የመጨረሻው ምእራፍ ላይ በመድረሱ በዚህ ክፍል ያልተሳኩልንን ችግሮች አቅርበናል።

### 2.1 <u>የሙሴ ተገኝን አፍራሽ እንቅስቃሴ ለማስቆም ያለመቻሉ፣</u>

ከአቀርብናቸው የመፍትሄ ሀሳቦች እንዱ ሙሴ ተገኝ በአስቸኳይ ከግንባሩ ካልለቀቀ በስተቀር ጉባኤ እንኳን ቢጠራ ትርጉም ያለው ለውጥ ሊመጣ እንደማይቻል ነበር። ከብዙ ወራት ዝምታ በኋላ የግንባሩ አመራሮች ከእኛ ጋር ግንኙነት በመፍጠር በጥናቱ ላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀሳቸውን በመግለጽ፤ የሙሴ ጉዳይም ሆነ የሌሎች አመራሮች እጣ ፋንታ ጉባኤ ተጠርቶ በሚደረግ ግምገማ እስከሚወሰን ድረስ፣ እስረኞችን የመፍታትና መስከረም አታላይን ወደ ግንባሩ ከልመጣ የማስወገድ እርምጃ እንዲወሰድ ወስነን ነበር። ይሁንና እስከ ጉባኤው ጊዜ ድረስ አለምአቀፍ ኮሚቲው ስለጉባኤ ዝግጅትና ሌሎች በጥናቱ የተዘረዘሩ ችግሮችን ለማቃለል በቀጥታ ከስራ አስፈሳሚ ኮሚቲዉ ጋር (ከሙሴ ውጭ ማለት ነው) እንዲሆን ለዚህም አስፈላጊው የመገናኛ መስመር ለማመቻቸት በራሳችን ወጭ እንዲከናወን ያቀረብናላቸውን ጥያቄ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም። በአሁኑ ጊዜ ሙሴ ተገኝ ከበፊቱ የበለጠ አድራጊ ፈጣሪ እየሆነ መምጣቱና፤ በጉባኤ ስም በራሱ አምሳል ሌላ ሴራ እዬጎነጎነ መሆኑን ሰለደረስንበት፤ የእስረኞችንም ሁኔታ በሚመለከት እርስ በራሱ የሚጋጭ ተልከሻ ምክንያት በመስጠት ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ በማንችልበት ደረጃ ላይ አድርሶናል።

## 2.2 ከኤርትራ መንግሰት ጋር በጋራ ጥቅም እና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲቀጥልና ኢሕአግ ኦፕሬሽናል ነጻነቱን ጠብቆ እንዲደረጅና እንዲንቀሳቀስ የተሞከረው ጥረት አለመሳካት፣

የጥናታችንን ዝርዝር ሪፖርት ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ከማስራጨት ባሻገር ተወከይ በመላክ ያቀረብናቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲደረጉ ትብብር በመጠየቅ በተገኘው የመገናኛ ዘዴ ሁሉ ሳንሰለች ስምንት ወራት ስንጎተጉት ቆይተናል፡፡

ሻቢያ ምንም እንኳን ኢሕአግን የማፈረሱንና የማዳከሙን ፖሊሲ አቅዶ፤ ለእቅዱ ተባባሪና ምቹ ሆነው ያገኛቸውን መስከረም አታላይን፤ ሙሴ ተገኝንና መልኬ መንግሰንቴ በመጠቀም ከ2004 ዓም ጀምሮ በረቀቀ መንገድ ተንኮል እየፈጸመ መሆኑን ብንረዳም፤ ከጊዜና ከታሪክ ተምረው ሊቀየሩ ይችላሉ በሚል በጎ አስተሳሰብና በተለይም ምርጫ 2005 ዓም ተከትሎ ወያኔ በሕዝባችን ላይ ያደረሰውን ግፍና ጭፍጨፋ መረጃ እያወጡ ለኢትዬጵያ ሕዝብ በአማርኛና በሌሎች ቋንቋዎች ተቆርቋሪ መስለው ሲያሰራጩ፤ጊዜና ነባራዊ ሁኔታ አስተምሯቸው ከኢትዬጵያ ሕዝብ ጎን ቆመዋል ብለን በመገመታችን ያቀረብነውን ማሻሻያ ሀሳብ ይቀበላሉ የሚል ተሰፋ ነበረን፡፡ ይሁንና የግንባሩን ሉዓላዊነት የጠየቀን ሁሉ እንደጠላት በመፈረጅ ንቃተ ህሊናቸው የበሰለ አርበኞችን በሰብ አስባቡ በማሰር፤ በማባረር እና ደብዛቸውን

በማጥፋት የኤርትራ የደህንነት ክፍል እጅ እንዳለበት ከአለፈው ታሪክ ብቻ ሳይሆን እኛ እራሳችን እንቅስቃሴ ከጀመርን ወዲህ በእነ ከሳሁን ሁንዴ ላይ የተፈጸመው እስራት እና አሁን ያሉበት ሁኔታ ያለመታወቅ በቂ ማስረጃ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የኤርትራ መንግስት ኢሕአግን በማዳከም እና በተጓዳኝ በቅርብ በእነ ሙሴ ፕሮግራም በብሄር ነጻ አውጭነት የተደረጁ ግንባሮችን ሳይቀር የማጠናከር ፖሊሲ ለብሄራዊ አንድነታችን ጠንቅ ከመሆኑ በላይ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለመዳን ሌላ የትግል አማራጭ እንዳይፈጠር አዘናጊ እና አደገኛ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የኤርትራ መንግስት በአሕአግ ላይ የፈጸመውን የማዳከም እርመጃ ዝርዝር ጥናታዊ ሪፖርት በቅርቡ እናቀርባለን፡፡

## 2.3. ያለአግባብ ለእስራት የተዳረጉ አርበኞች እንዲፈቱ የተደረገው ጥረት አለመሳካት

ዓለምአቀፍ ኮሚቴው አጥንቶ ያቀረባቸውን የመሻሻያ ነጥቦች ወደ ተግባር ለመተርጎም በኤርትራ መንግስት ተጽእኖና ግንባሩን ለማደከም መርጦ ባስቀመጣቸው የኢሕአግ መሪዎች ምክንያት ተግበራዊ ማድረግ እንደማይቻል ገና ጥናቱን እንደ አጠናቀቅን የተገነዘብነው ጉዳይ ቢሆንም፣ እንደተገፋን እያወቅን ተለሳልሰን የግነኙነት መስመሩ እንዳይበጠሰ የጣርነው እንዱ ምክንያት በእስር ላይ በሚገኙ አርበኞች ሕይወት ላይ አደጋ አድንዳይደርስ በመስጋት በዲፕሎማሲያዊ ግፊት እንዲፈቱ ጥረት ለማድረግ ነበር፡፡

በጣም የሚያሰገርመው ነገር የእኛ ኮሚቴ እስረኞችን ለማስፈታት ሲጥር፤ በሌላ በኩል ከኮሚቴያችን አፈንግጠው መስከረም አታላይን አጅበው የሄዱት የቀድሞ አመራር አባሎች ኤርትራ ድረስ ልዑክና ጋዜጠኛ ልከው የታሰሩትን አርበኞች ከእኛ ጋር ተባባሪ ሆነው ለማፈንገጥ የሞከሩ ናቸው በማለት የእነርሱን ታማኝነት ለማረጋገጥ በወንድሞቻቸው ላይ ፈርደውባቸዋል፡፡ መስከረም እና ተከታዮቹ በየመድረኩ «ትግል ነውና ሊረሸኑም ይችላሉ» በማለት ያለ ሀፍረት በድፍረት ሲናገሩ መደመጣቸው የአደባባይ ምስጢር ነበር፡፡

በመጨረሻም የግንባሩ አመራሮች በስልክና በቲሌ ኮንፈረስ የታሰሩ አርበኞች በሙሉ መለቀቃቸውንና ለሌሎች በጥናታችን ላይ ያቀረብናቸውን መሻሻያዎች ደረጃ በደረጃ መፍተሄ ለመስጠት መጀመራቸውን በይፋ መስከረም አታላይን በማስወገድና ጉባኤ ለመጥራት በመወሰን እርምጃ ሲወስዱ፤ በእውነት ተቀብለንና አምነናቸው አስረኞች እንደተፈቱ የተነገረን መሆኑን በድረገጽአችን በ ጁላይ 14 ቀን 2007 ዓም ይፋ አድርገን ነበር:: የተጀመረውን ግንባሩን የማስተከከል እርምጃ በአካል ተገኝተን ለማረጋገጥ የኮሚቴያችን እንድ አባል ወደ ግንባሩ ለመላክ ዝግጅት በማድረግ ላይ እያለን፤ ተፈቱ የተባሉተ አርበኞች በሕይውት የሉም፤ የሚል መረጃ ከሌላ ጎረቤት ሀገር ሲደርሰን፣ በድንጋጤ ለሙሴ ተገኝ በመደወል የተፈቱት አርበኞችን በአርበኛ ድምጽ ራዲዮ ቃለ ምልልስ እንዲሰጡን ጠየቅን፤ የሙሴ መልስ አርበኞቹ ከተፈቱ በኋላ ወደ አገራችን እንመለሳለን ስላሉን ወደ ጎረቤት ሀገር ሸኝተናቸዋል ልናገናኛችሁ አንችልም ነበር:: የተሰጠን መልስ ይበልጥ ስለአስደነገጠን የግንባሩን ጊዚያዊ ሊቀመንበር አርበኛ መዓዛን እንዲያቀርብልን ባደረግነው ጉትጎታ ኦገስት 25/2007 ዓም አብዛኛው የአለምአቀፍ ኮሚቲ አባል በተሳተፉበት ቲሌ ኮንፈረስ ላይ ተፈቱ ስለተባሉት እስረኞች ደህንነት ቃለ ምልልስ ከአደረግን በኋላ የሚከተሉትን እውነታዎች እንድንረዳ አድረገውናል::

ሀ. አርበኛ መአዛ ለእኛ የገለጸልንና ሙሴ ተገኝ በግል ተጠይቆ የሰጠን መልስ በጣም የተራራቀ ሆኖ አግኝተነዋል::

ለ. ተፈቱ የተባሉበት ወቅት መስከረም አታላይ ከመውረዱ በፊት ስለነበርና ውሳኔው ተሰጠ የተባለው በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው (መስከረምም ያለበት) ስለሆነ በውሳኔው ላይ የመስከረም እጅ እንደነበረበት አስገንዝቦናል::

ሐ. ተአምር ከልተፈጠረ በስተቀር ከሶስት ወራት በፊት በዚህ ሁኔታ የተፈቱ አርበኞች በሕይወት አሉ ብለን እንድናስብ ተስፋ የሰጠን ሁኔታ የለም::

መ. የግንባሩ ከዚህ በፊት በነ ተስፋዬ ጌታቸውና በሌሎችም ላይ የፈሰመውን አሰቃቂ ታሪክ ስናስታውስ መስከረም አታላይ በየመድረኩ፤ እነ ከሳሁን ሁንዴ ሊረሸኑ ይችላሉ እያለ የዛተባቸውን ስናስተውል ወንድሞቻችን አደጋ ላይ ወድቀዋል ብለን እንድናስብ አስገድዶናል::

ከላይ በሶስት የተለያዩ ክፍሎች በዘረዘርናቸው ምክንያቶች (የሙሴ ተገኝ ተጽእኖ፤ የኤርትራ መንግስት ግንባሩን የማዳከም ፖሊሲ የታሠሩ አርበኞች ደህንነት ባልታወቀበት ሁኔታ) ግንባሩ ጉባኤ ለመጥራት ፈቃደኛ ነኝ ቢልም፤ ችግር አስወጋጅ ጉባኤ እንደማይሆን ተገንዝበነዋል::

## <u>ክፍል 3፤</u>

### <u>የኢ.ሕ.አ.ግ አለምአቀፍ ኮሚቴ ውሳኔዎችና ቀጣዩ የትግል አቅጣጫ</u>

ኮሚቴአችን በአንድ በኩል ያለመታከት በትእግስት ባደረገው ትግልና ጫና በኢሕአግ አመራር ዙሪያ የተገኙ በጎ ውጤቶችን፤ በሌላ በኩል የቱንም ያክል ብንለፋና ብንታገል ግንባሩ ሊያስተከክል ያልቻላቸውን (በክፍል 2 የተዘረዘሩ ችግሮችን) በማመዛዘን በኢሕአግ እጣ ፋንታና የወደፊት የትግል አቅጣጫ ላይ ከፍተኛ ጥናታዊ ግምገማ ከአደረግን በኋላ የሚከተለውን ውሣኔዎች ወስነናል:-

ሀ. ኢሕአግ አገርንና ሕዝብን ለመታደግ ብለው እራሳቸውን፤ ትምህርታቸውን፤ ሥራቸውንና የሚወዶቸውን ቤተሰብ እርግፍ አድርገው ለትግል የተዘጋጁ ቆራጥ አርበኞች ያጣ ድርጅት ባይሆንም፤ መስዋትነታቸው ውጤት እንዳያመጣና ዋጋ እንዳይኖረው ሌት ከቀን ሴራ በሚጠነስሱና በሚያሰናክሉ ራስ ወዳድና ከሃዲ

አመራሮች ሆን ተብሎ የተተበተበ በመሆኑ፤ የኤርትራ መንግስትም የሴራው ጠንሳሽና ፈጻሚ በመሆን በርከታ የነቁ አርበኞችን ለእስራትና በረቀቀ ዘዴ ከማጥፋት አሁንም እንዳልተቆጠበ በቅርቡ ከአለምአቀፍ ኮሚቴ አባሎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥራቸኋል ተብለው፤ ሰበብና ወጥመድ ተዘጋጂቶላቸው ሰእስር ከተዳረጉ በኋላ በአሁኑ ሰአት የደረሱበት ያልታወቀ አርበኞች እነከሳሁን ሁንዴ ላይ መፈጸሙን በተግባር ለመመልከት ችለናል።

የአርበኞች ደህንነት አደጋ ላይ በወደቀበት ሁኔታ የግንባሩን ነጻነት መጠየቅ እንደ ጸረ-ኤርትራ አቋም ተደርጎ የሕይወት መስዋዕትነት በሚያስከፍልበት ሁኔታ ትግሉን በኤርትራ መስመር መቀጠሉ አዘናጊና ለኢትዮጵያዉያን አደገኛ ሆኖ ስለአገኘነዉ ይህ መግለጫ በይፋ ከወጣበት ከኦገስት 30 ቀን 2007 ጀምሮ ኤርትራ ከሚገኘዉ የኢ.ሕ.አ.ግ አመራር ጋር ግንኙነታችን እንዲቋረጥ ወስነናል።

ለ. ኮሚቴያችን ከስምንት ወራት በፊት የኤርትራ መንግስት በኢ.ሕ.አ.ግ አመራር ላይ ተጽእኖ ማድረጉን የሚያመለክቱ ሁኔታች መኖራቸዉን እንደተረዳ የትግሉን አቅጣጫና ስትራቴጂ ለመቀየር እራሱን የቻለ ዲፓርትመንት አቋቁሞ ጎን ለጎን በርካታ አማራጮችን ሲያጠናና ሲያዘጋጅ ቆይቷል። በመሆኑም ከአሁን ወዲያ አገርን ለማዳን የሚደረገዉ ትግል በአገር ዉስጥና ከኤርትራ ዉጭ እንዲደራጅ የጀመርነዉን ጥረት በተጠናከረና በተቀናጀ መልክ ለመቀጠል ወስነናል።

ሐ. በነሙሴ ተገኝ፣ መስከረም አታላይና የኤርትራ መንግስት የደህንነት ክፍል ያለ አግባብ ለበርካታ ወራቶች ከታሰሩ በኋላ አሁን የደረሱበት ያልታወቁ አርበኞች ማለትም፣አርበኛ ካሳሁን ሁንዴ፣ አርበኛ መምህር ጌታቸዉ ወርቅነህና ሌሎችም በወያኔ ግፍ ተፈጽሞባቸዉና አካላቸዉን ጎድሎ ኢ.ሕ.አ.ግን የተቀላቀሉ ወገኖች ትናንት በነተስፋዬ ጌታቸዉ ላይ የተፈጸመዉ ግፍ ተሰርቶባቸዉ ከሆነ ዛሬ አርበኛዉ እንደ ትናንቱ ብቻዉን አይደለምና የሚያስከትለዉ መዘዝ ቀላል አይሆንም። ከሁሉም በላይ በሁለቱ ሕዝቦች (ኢትዮጵያና-ኤርትራ) መካከል በየዋህነት ሳይሆን በበጎ ናፋቂዎች ጥረት ጤናማ መቀራረብ እንዲፈጠር የተደረገዉን ጥረት ሁሉ የሚያፈርስ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት ቆመናል ብለዉ መግለጫ በይፋ የሰጡትን የፓለቲካ መሪዎች በተግባር የሚፈታተን በመሆኑ፣ የኤርትራ መንግስት ከእስር ተፈትተዋል የተባሉትን አርበኞች ደህንነት ለማረጋገጥ እስከ ሴፕቴምበር 10 ቀን 2007 አርበኞች «በአርበኛ ድምጽ ሬዲዮ» ለማቅረብ እንዲተባበረን በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም በደብዳቤ እንዲጠየቅና ዉጤቱ ለሕዝብ በይፋ እንዲገለጽ ወስነናል።

መ. ቀጣዩን የትግል አቅጣጫ፣አደረጃጀት፣መዋቅርና ራዕይ በተመለከተ ዓለምቀፍ የዉጭ ኮሚቴዉ የአባላትና ደጋፊች ጉባኤ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ በመጥራት ተወያይቶና ገምግሞ፣ ሌሎች ለትግሉ ተቆርቋሪ ከሆኑ ወገኖችና ድርጅቶች ጋር ምክክር አድርጎ የሚደርስበትን ዉጤት ለሕዝብ በይፋ እንዲገለጽና ትግሉ በተደራጀና በተጠናከረ መንገድ እንዲቀጥል ተወስኗል።

አንድነት ኃይል ነዉ!!!
የኢትዩጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር አለምአቀፍ ኮሚቴ
www.eppf.info